# 2017 “ሁለተኛው ዝቅተኛው ወጪ ሲልቨር ፕላን”(“Second Lowest Cost Silver Plan”) ወጪዎች

በአፎርዳብል ኬር አክት (Affordable Care Act) ስር፣ ፕሪምየም ታክስ ክሬዲት ዝቅተኛ እና መሀከለኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች በዲሲ ሄልዝ ሊንክ በኩል ሁለገብ(ኮምፕሪሄንሲቭ) የጤና ኢንሹራንስ ለማግኘት እንዲችሉ የመክፈል አቅማቸውን ለመርዳት ታቅዶ የተዘጋጀ ነው። ክሬዲቱ ከጤና ኢንሹራንሱ ቤንች ማርክ ፕላን ወርሃዊ ክፍያው(ፕሪምየሙ)ላይ ከቤተሰቡ ገቢ ፐርሰንቴጅ የሚያልፈውን ያህል ይሸፍናል። ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች ያነሰ ክሬዲት ያገኛሉ። ቤንችማርክ ፕላኑ (The Benchmark Plan) በዲሲ ሄልዝ ሊንክ ገበያ በኩል የሚቀርብ ሁለተኛው ዝቅተኛው ወጪ ያለው ሲልቨር ፕላን ነው።

የቤንችማርክ ፕላን ወጪው በምዝገባው ወይም ማሳደሻው ወቅት እያንዳንዱ ተመዝጋቢ ያለበት እድሜ ላይ ተመስርቶ ይለያያል። ለ 2017፣ የዲሲ ሄልዝ ሊንክ ቤንችማርክ ፕላን (DC Health Link Benchmark Plan) ብሉ ቾይዝ ኤችኤምኦ ስታንዳርድ ሲልቨር (*BlueChoice HMO Standard Silver)$2000* ነው፣ እና በቤት ውስጥ ላለው እያንዳንዱ ቤተሰብ የወርሃዊ ክፍያው (ፕሪምየሙ) እንደሚከተለው ነው:

| እድሜ | ወርሃዊ ክፍያ(ፕሪምየም) |
|---|---|
| አዲስ የተወለደ እስከ 20 አመት | $ 198.47 |
| ከ 21 – 27 አመት | $ 220.63 |
| 28 አመት | $ 225.79 |
| 29 አመት | $ 230.65 |
| 30 አመት | $ 236.41 |
| 31 አመት | $ 242.48 |
| 32 አመት | $ 247.94 |
| 33 አመት | $ 253.71 |
| 34 አመት | $ 259.78 |
| 35 አመት | $ 265.85 |
| 36 አመት | $ 271.92 |
| 37 አመት | $ 277.98 |
| 38 አመት | $ 281.33 |
| 39 አመት | $ 284.67 |
| 40 አመት | $ 295.89 |
| 41 አመት | $ 307.42 |
| 42 አመት | $ 319.56 |
| 43 አመት | $ 332.00 |

| እድሜ | ወርሃዊ ክፍያ(ፕሪምየም) |
|---|---|
| 44 አመት | $ 345.06 |
| 45 አመት | $ 358.41 |
| 46 አመት | $ 372.37 |
| 47 አመት | $ 386.93 |
| 48 አመት | $ 402.11 |
| 49 አመት | $ 417.89 |
| 50 አመት | $ 434.28 |
| 51 አመት | $ 451.28 |
| 52 አመት | $ 468.88 |
| 53 አመት | $ 487.09 |
| 54 አመት | $ 506.20 |
| 55 አመት | $ 525.93 |
| 56 አመት | $ 546.57 |
| 57 አመት | $ 567.81 |
| 58 አመት | $ 589.96 |
| 59 አመት | $ 613.02 |
| 60 አመት | $ 637.00 |
| 61 እና ከዚያ በላይ አመት | $ 661.89 |

ከታክስ ቤተሰቡ መሀከል ከአንድ በላይ የሆኑ ግለሰቦች በዲሲ ሄልዝ ሊንክ ፕላን ውስጥ የሚመዘገቡ ከሆነ፣ እና ከሌላ ቦታ ሽፋን ለማግኘት የማይቻል ከሆነ(ለምሳሌ፣ ሜዲኬድ፣ ሜዲኬር፣ ቀጣሪ ስፖንሰር የሚያደርገው ኢንሹራንስ)፣ የቤንችማርክ ፕላን ወጪው የእያንዳንዱ አባል ፕሪምየም ድምር ነው።

ምሳሌ 1

ጆ አላገባም እና ታክሱ ላይ ምንም ጥገኛ(ዲፔንዳንት) አያስገባም። ለአድቫንስድ ፕሪምየም ታክስ ክሬዲት ብቁ ነው ምክንያቱም ለሜዲኬድ ወይም ሌላ ከዲሲ ሄልዝ ሊንክ ውጪ ለሆነ ሽፋን ብቁ አይደለም። እድሜው 30 አመት ነው ስለዚህ የቤንችማርክ ፕላን ፕሪምየሙ(ወርሃዊ ክፍያው) $236.41 ነው።

ምሳሌ 2

ማርክ እና ሉሲ ተጋብተዋል እና ታክሳቸው ላይ ምንም ጥገኛ(ዲፔንዳንት) አያስገቡም። ሁለቱም ለአድቫንስድ ፕሪምየም ታክስ ክሬዲት ብቁ ናቸው ምክንያቱም ለሜዲኬድ ወይም ከዲሲ ሄልዝ ሊንክ ውጭ ለሆነ ሌላ ሽፋን ብቁ ስላልሆኑ።ማርክ እድሜው 25 አመት ነው እና ሉሲ 28 አመቷ ነው፣ እና ስለዚህ የቤንችማርክ ፕላን ፕሪሚይማቸው(ወርሃዊ ክፍያቸው) $446.42 ($220.63 + $225.79) ነው።

ምሳሌ 3

ጄሪ እና አናቤላ ተጋብተዋል እና ታክሳቸው ላይ ምንም ጥገኛ አያስገቡም። አናቤላ ነፍሰ-ጡር ናት እና ለሜዲኬድ ብቁ ናት። ጄሪ ለሜዲኬድ ወይም ከዲሲ ሄልዝ ሊንክ ውጭ ለሆነ ለሌላ ሽፋን ብቁ አይደለም። ጄሪ 25 አመቱ ነው እና አናቤላ 23 አመቷ ነው። ነገር ግን ጄሪ ብቻ ነው ለአድቫንስድ ታክስ ክሬዲት ብቁ የሚሆነው ምክንያቱም አናቤላ ሽፋን ለማግኘት ስለቻለች ነው(ሜዲኬድ)። ስለዚህ ቤንችማርክ ፕላን ፕሪሚይማቸው(ወርሃዊ ክፍያቸው) $220.63 ነው።

ምሳሌ 4

ፍራንክ እና ሜሪ ተጋብተዋል እና ታክስ ክሬዲት ላይ እንደ ጥገኛ የሚሞሏቸው ሉክ የሚባል ወንድ ልጅ እና ሄዘር የምትባል ሴት ልጅ አላቸው። ሉክ ልጅ እንደመሆኑ ለሜዲኬድ ብቁ ነው። ሌሎቹ ለሜዲኬድ ወይም ሌላ ከዲሲኤችኤል (DCHL) ውጪ ለሆነ ሽፋን ብቁ አይደሉም። ፍራንክ 45 አመቱ ነው፣ ሜሪ 43 አመቷነው፣ ሉክ15 አመቱ ነው እና ሄዘር 19 አመቷነው። ስለዚህ፣ የቤንችማርክ ፕላን ፕሪምየማቸው $888.88 ($358.41 + $332 + $198.47) ነው። እንደገና፣ ሉክ ወደ ቤንችማርክ ፕላን ላይ አይገባም ምክንያቱም ለሌላ ሽፋን ብቁ ነው(ሜዲኬድ) እናም ለአድቫንስድ ፕሪምየም ታክስ ክሬዲት ብቁ አይደለም።

ምሳሌ 5

ሄንሪ እና ኤልዛቤጥ ተጋብተዋል እና ልጃቸው ኤድዋርድን ታክስ ላይ እንደ ጥገኛ ያስገባሉ(ክሌም ያደርጋሉ)። ሄንሪ 55 አመቱ ነው፣ ኤልዛቤጥ 53 አመቷ ነው እና ኤድዋርድ 28 አመቱ ነው።ሄንሪ በቀጣሪው በኩል ሽፋን ለማግኘት ብቁ ነው እና ኤልዛቤጥም በባለቤቷ በኩል ተመሳሳይ ሽፋን ለማግኘት ብቁ ናት። ኤድዋርድ በቀጣሪው በኩል ላለው ለሽፋ ብቁ አይደለም ምክንያቱም ልጅ ሆኖ ለመግባት እድሜው ትልቅ ነው። ማናቸውም ለሜዲኬድ ብቁ አይደሉም። ስለዚህ፣ ለአድቫንስድ ፕሪምየም ታክስ ክሬዲት ብቁ የሚሆነው ኤድዋርድ ብቻ ነው እና የቤተሰቡ ቤንችማርክ ፕላን ፕሪምየም $225.79 ነው። ይህ ሄንሪ ወይም ኤልዛቤጥ ቀጣሪ-ስፖንሰር የሚያደርገው ኢንሹራንስ ላይ ባይመዘገቡም እንኳን የሚሆን ነው።